በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1991 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 1991

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1991 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሚያዝያ 1991

# ማ ው ጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ | 2 |
| 2.1 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ | 3 |
| 2.2 ሕዝብን በተመለከተ ሌሎች ጥናቶችና ተዛማጅ ሥራዎች | 3 |
| 2.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች | 5 |
| 3. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 5 |
| 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | 6 |
| 3.2 የሰው ኃይል የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናትን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 9 |
| 3.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ | 13 |
| 3.4 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት | 14 |
| 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ | 17 |
| 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 17 |
| 4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 17 |
| 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ | 18 |
| 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና | 19 |
| 6.1 የሰው ኃይል ሁኔታ | 19 |
| 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠና | 21 |
| 7. የበጀት አጠቃቀም | 22 |
| ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም | 22 |
| ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም | 23 |
| 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት | 24 |
| 8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 24 |
| 8.2 የዕቃዎች ጥገናን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 25 |
| 8.3 የመኪና ሥምሪትና ጥገናን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 26 |
| 8.4 የኢንሹራንስ አገልግሎትን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት | 26 |
| 8.5 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች | 27 |
| 9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ እርጃዎች | 29 |

# የ1991 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት
# የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የአሁኑ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሀገሪቱን ስታቲስቲካዊ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ በየጊዜው አቅም በፈቀደ መጠን የተቻለውን ሁሉ ሲያከናውን መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሠረት በርካታ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊና የሥነ-ሕዝብ ጥናቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ከማካሄዱም በተጨማሪ በ1976 የመጀመሪያውን ፣ በ1987 ሁለተኛውን መላው አገሪቱን የሸፈነ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አካሂዶ የሁለቱንም ውጤትና የሌሎችም ተመሳሳይ ጥናቶች ውጤት ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል፡፡ የእነዚህንና የሌሎችም መ/ቤቱ ያሰራጫቸው ሪፖርቶች ለልዩ ልዩ ሥራዎች ተጨባጭ መነሻ በመሆን ጥቅም ላይ ውለዋል፣ በመዋልም ላይ ናቸው፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በ1991 በጀት ዓመት ለስታቲስቲክስ መረጃ ሀብት መጎልበት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ አሥር ዓይነት ጥናቶች ለማካሄድና ሌሎች ነባር ጥናቶችም ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የመንገድና ትራንስፓርት ስታቲስቲክስ የሙከራ ጥናት (በገጠርና በከተማ) በጥናቶች መደራረብም ምክንያት በ1991 በጀት ለማካሄድ አልተቻለም፡፡ ሆኖም በመንግሥት በኩል በተሠጠው ውሣኔ መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ በገጠርና በከተማ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በተጨማሪ እንዲካሄድ ተደጓል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የተካሄዱና በመካሄድ ላይ ያሉ ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት (በገጠር)
2. የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናት (በገጠር)
3. የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ( በከተማ)
4. የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ የሙከራ ጥናት (በከተማ)
5. የሰው ኃይል ጥናት (በገጠርና በከተማ)
6. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ( በከተማ)
7. የኮንስትራክሽን እንቅስቃሴ አጠቃላይ ቆጠራ (በከተማ)
8. የማዕድንና ቁፋሮ የሙከራ ጥናት (በከተማ)
9. የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት (በገጠርና በከተማ)
10. የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት ናቸው፡፡

በእነዚህ ጥናቶች ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል ቢሆንም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ማለትም ከሐምሌ 1/1990 እስከ

መጋቢት 30/1991 ድረስ የጥናቶቹ የዝግጅት ተግባር ተከናውኖ የዋና ዋናዎቹ ጥናቶች መረጃ የመሰብሰብ ሂደት በአብዛኛው ተጠናቋል:: ከነዚህም ውስጥ እስከ መጋቢት 30/1991 ድረስ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ በኮምፒውተር ተጠናቅሮ ሪፖርቱም ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን የግብርና ናሙና ጥናት መረጃው ተሰብስቦ የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ እንደዚሁም የቬሪፊኬሽን ሥራ በማጠናቀቅ የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃም በኮምፒውተር ተጠናቅሮ የሪፖርትም ዝግጅት ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል:: የቀሩት የ1991 የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናቶች ቅንብርም እየተካሄደ ነው:: በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት በተለይም በ1990 በጀት ዓመት ከተካሄዱት ጥናቶች መካከል የአንዳንዶቹ የመረጃ ቅንብርና የሪፖርት ዝግጅት ሥራዎች በዚህ ዘመኝ ወራትም ቀጥሎ እየተከናወነ ነው::

በ1991 በጀት ዓመት ለማካሄድ የታቀዱት ጥናቶች አፈጻጸምን አስመልክቶ ቀደም ሲል በ1990 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር ተዘጋጅቶ በተላለፈው መርሀ-ግብር መሠረት በአብዛኛው ተግባራዊ እየሆነ ነው:: ሆኖም ከሰው ኃይልና ከሎጅስቲክስ ስምሪት አንጻር የመ/ቤቱን የማስፈጸም አቅም በመገምገም አንዳንድ ጥናቶችን በማሸጋሸግ ተስማሚ ወቅትና ጥሩ ቅንጅት የሚፈጠርበት ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል::

ይህ ሪፖርት በ1991 የዘጠኝ ወራት ውስጥ የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፣ ስለ ሰው ኃይል ሁኔታና ስለ በጀት አጠቃቀም የሚያመለክት አኃዛዊ መረጃዎች ይዟል:: በተጨማሪም በዘጠኝ ወራት ውስጥ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ የታዩ ችግሮች እንደዚሁም መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይችል ዘንድ ከበላይ አካል ትኩረት ተሰጥቶአቸው መፍትሔ የሚሹ አጠቃላይ ችግሮች በሪፖርቱ መጨረሻ ክፍል እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በሌሎች ዘርፎች ያለውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ያላሰለሰ እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ ሁሉ የሕዝብና ቤቶችን መረጃ በተመለከተም ሁለቱ አገር አቀፍ የሆነ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች አካሂዶ በርካታ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች አሠራጭቷል:: በተጨማሪ በተለያየ ወቅት ሕዝብ-ነክ ጥናቶች እያካሄደ ውጤቱን ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል:: በመሆኑም በዚህ የዘጠኝ ወራትም ጊዜ ውስጥ የሕዝብና ቤቶች ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል::

## 2.1 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ

ሀ. የሁሉም ብሔራዊ ክልሎችና መስተዳድሮች የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ስታቲስቲካል ሪፖርቶች ቀደም ሲል ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል:: በዚህ ዘመኝ ወራት ደግሞ የሁሉንም ክልሎችና መስተዳድሮች የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ አጠቃሎ የያዘና በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ ስታቲስቲካል ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

ለ. የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝና የጋምቤላ ብሔራዊ ክልሎች አናሊቲካል ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል:: የሐረሪ፣ የአዲስ አበባና የድሬደዋ የቆጠራ አናሊቲካል ሪፓርቶች ዝግጅትም ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታም የአፋርና የሶማሌ ብሔራዊ ክልሎች አናሊቲካል ሪፓርቶች ደግሞ ተጠናቅረው ለሕትመት ዝግጁ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አጠቃላይ አገሪቷን የሚመለከት አናሊቲካል ሪፓርት ዝግጅትም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል::

ሐ. አጠቃላይ የአገሪቷን የቆጠራ ውጤት የሚያመለክቱ መረጃዎች በግራፎችና በቀላል ጽሑፎች (ለፖሊሲ አርቃቂ በሚያመች መልክ) ተዘጋጅቶ የሕትመት ሥራው ተጠናቋል::

## 2.2 ሕዝብን በተመለከተ ሌሎች ጥናቶችና ተዛማጅ ሥራዎች

### 2.2.1 የቫይታል ስታቲስቲክስ ናሙና ምዝገባ ጥናትን በተመለከተ

ሀ. የቫይታል ስታቲስቲክስ ናሙና ምዝገባ ጥናት የመጀመሪያ ዙር መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በመጠናቀቁ የኤዲቲንግና የኮዲንግ ሥራው በመ/ቤቱ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ተከናውኗል:: መረጃውንም በኮምፒዩተር ለማቀነባበርና ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ይረዳ ዘንድ Tabulation Plan and Summary Table ተዘጋጅቷል:: በተዘጋጀውም Computer Edit Specification መሠረት የዳታ ኢንትሪው ሥራ ከመጠናቀቁም ሌላ Cross Tabulation ሠርቶ ለማቅረብ Raising Factor በ Methodology በኩል ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል::

ለ. የቫይታል ስታቲስቲክስ ናሙና ምዝገባ የመጀመሪያው ስድስት ወር መረጃ የተሞላባቸው መጠይቆች ወደ ዋናው መ/ቤት በማሰባሰብ የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራቸው ተከናውኗል:: የቫይታል ምዝገባው የመጀመሪያ ዙር ጥናትና በመጀመሪያ ሦስት ወር የምዝገባ ሪፖርት ተገምግሞ በታየው ችግር መሠረት የመ/ቤቱ አባላት ወደ መስክ ሄደው ችግሩን እንዲፈቱት ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ ለሁለተኛ ዙር ጥናት እንዲያገለግል የተሻሻለ መመሪያ ከመዘጋጀቱም ሌላ ለBirth and Death Events Matching መመሪያ በመዘጋጀት ላይ ነው::

ሐ. በሀገሪቱ የቫይታል አመዘጋገብ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያመቻቹ አዳዲስ ሀሳቦችን ያካተተ ጽሑፍ ተዘጋጅቷል:: በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ የተደረገውን ማሻሻያ በማካተት ሁለተኛ ረቂቅ ለባለሙያዎች ተበትኖ ግምገማው እየተካሄደ ነው:: በዚህ ወቅት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ የሚቀርብ ጥናታዊ ጽሑፍ የረቂቅ ሀሳብ እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል:: ይህንኑ የምዝገባ ሥርዓት አወቃቀርን አስመልክቶ የወቅቱ የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠትና በዚሁ አካባቢ ለሚነሱ ጥያቄዎች ለመመለስ በሚያስችል መልኩ ጥናትና ዝግጅት እየተደረገ ነው::

### 2.2.2 የጤናና የአመጋገብ ጥናትን በተመለከተ

ከሐምሌ 15 ቀን እስከ ነሐሴ 15/1990 ዓ.ም. ድረስ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የጤናና የአመጋገብ ጥናት መረጃዎች ላይ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተከናውኗል:: በተመሣሣይ ሁኔታ የዳታ ኢንትሪው ሥራም እስከ መስከረም 25/1991 ዓ.ም. ድረስ ሙሉ በሙሉ ከመጠናቀቁም በተጨማሪ የTabulation plan እና Edit Specification በወቅቱ ተዘጋጅቷል:: በዚሁ መሠረት ለመረጃ ትንተና የሚያስፈልጉ ሠንጠረዦች የመጀመሪያ ድራፍት ተዘጋጅቶ አስፈላጊው እርማት ተደርጓል:: በመጋቢት ወር ተዘጋጅቶ በቀረበው የመጀመሪያ ድራፍት ሪፓርት ላይ ውይይቶች የተደረገ ሲሆን በውይይቱም የተሰጡ አስተያየቶችና እርማቶች በሪፓርቱ ላይ እንዲካተቱ የሚደረግ ቢሆንም በዚህ በኩል የሚደረግ ውይይት ግን ባለመጠናቀቁ በቀጣይነት ይካሄዳል::

## 2.3. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ጉዳይ ፈንድ (UNFPA) ለመጪዎቹ አራት ዓመታት ለሚሰጠው ዕርዳታ ንዑስ ፕሮግራሞች "በሥነ-ሕዝብና ልማት" የንዑስ ፕሮግራም ዝግጅት ላይ ከተለያዩ መ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ባሉበት የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል አባላት በዝግጅቱ በመሳተፍ ላይ ናቸው::

ለ. በ1996 ዓ.ም. ሊካሄድ ለታሰበው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የካርታ ሥራ በኮምፒዩተር ለማገዝ ይቻል ዘንድ በUNFPA በኩል አንድ የኮምፒዩተር ማፒንግ ኤክስፐርት እንዲመጣ ተደርጓል:: ይኸው ኤክስፐርት ለካርታው ሥራ አገልግሎት የሚውል ዕቃ ግዢና የሥልጠና ተግባራት የሚካሄድበትን ስልት ቀይሷል::

ሐ. ከመዛግብት የሚገኙ መረጃዎች ( Secondary Data )ን በተመለከተ መረጃ ሰጪ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የተገኙት መረጃዎች በማጥራትና በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ላይ በታዩ ችግሮች መፍትሔ በመሻቱ ሂደት ላይ ውይይት እየተደረገ ነው::

# 3. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በኢኮኖሚና ማህበራዊ ስታቲስቲክስ በኩል ያሉትን መረጃዎች ይዘት በሁሉም መልኩ ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት የተለያዩ ጥናቶች ለማካሄድ አቅዷል:: ከነዚህም ውስጥ 4 ነባርና 5 አዳዲስ ጥናቶች ይገኙበታል:: ከነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ በ1990 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው ተጠናቆ የመረጃ ማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት ሥራቸው ወደ 1991 የተሸጋገሩ የተወሰኑ ጥናቶች የማጠናቀቁ ተግባር ይካሄዳል:: በተጨማሪም ከመንግሥት በተሰጠው መመሪያ መሠረት የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የመጀመሪያውን ዙር በሰኔ ወር 1991 ዓ.ም ለማካሄድ የዝግጅት ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል::

በሌላ በኩል በ1991 በጀት ዓመት እንዲጠኑ በዕቅድ ተይዘው ከነበሩት ነባር ጥናቶች ውስጥ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት አንዱ ነበር:: ነገር ግን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት በዚህ ዓመት ስለማይጠናና በዚህ ፋንታ

በከተሞች የአምራቾች ዋጋ የሙከራ ጥናት እንዲካሄድ ተወስኖ የነበረ ቢሆንም በፕሮግራም መደራረብና በሥራ ውጥረት ምክንያት ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል ሆኖም ከዚህ ጥናት የሚገኘው ተፈላጊ መረጃ ዓመታዊ ዋጋ የሚያሳዩ መረጃዎች ከማምረቻ እንዱስትሪዎች ጥናት እንዲሰበሰብ በመደረጉ መረጃው ተሰብስቦና ተቀነባብሮ ለሚመለከታቸው መረጃ ተጠቃሚዎች ተሰጥቷል:: በመሆኑም በዚህ የዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ በተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የታቀፉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናቶችና የሌሎች መደበኛ ጥናቶች የዕቅድ አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ በታች ቀርቧል::

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

የ1991 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ጥራቱን በመስክ ተገኝቶ ለመከታተል የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ጥናቱ በሚካሄድባቸው ቦታዎች በመዘዋወር የግምገማና የቁጥጥር ተግባር አከናውነዋል:: የዚህ ጥናት መረጃም ከመስክ ወደ ዋናው መ/ቤት ከተሰባሰበ በኋላ ለመረጃው ጥራትና ቅንብር የሚረዱ የእርማት ፣ የኮድ መስጠትና የቅንብሩ ሥራ በኮምፒውተር በአንደ ወር ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ውጤቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

### ለ. የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃን በተመለከተ

- የ1990 ዓ.ም. የግብርና ናሙና ጥናት ውጤት የሆነውን የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ የያዘ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

- የ1990 ዓ.ም በበልግ ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና የምርቱ መጠን መረጃ የኮምፒውተር ቅንብሩና የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተጠናቆ በመታተም ላይ ይገኛል::

- የ1991 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት ጥናት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን መረጃ አስፈላጊው የኮምፕዩተር ቅንብር ሥራና የሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ በመታተም ላይ ይገኛል::

ሐ. **የእርሻ ሥራ (Farm Management Practices) መረጃን በተመለከተ**

- የ1990 ዓ.ም. የመኸር ወቅት እርሻ ሥራ መረጃ የቅንብሩ ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1990 ዓ.ም. የበልግ ወቅት የእርሻ ሥራ መረጃም የማቀነባበሩ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የሪፖርት ዝግጅቱም በመሰራት ላይ ይገኛል።

- የ1991 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ከመስክ ወደ ዋናው መ/ቤት ተሰብስቦና የመጀመሪያ ደረጃ ሠንጠረዥ ቅንብሩ ተጠናቆ የመረጃው ትክክለኛነት በመገምገም ላይ ነው።

መ. **የመሬት አጠቃቀምን (Land Utilization) በተመለከተ**

- የ1990 የመሬት አጠቃቀም መረጃ የቅንብሩ ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- በዚሁ ሪፖርት የ1991 መረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ሠንጠረዥ ቅንብር ተጠናቆ መረጃው በመገመገም ላይ ይገኛል።

ሠ. **የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ**

- የ1990 የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሀብትና የንብ ቀፎዎች የመረጃ ቅንብር እና የሪፖርት ዝግጅቱ ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1991 የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሀብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ነው።

ረ. **ሌሎች የተከናወኑና በመከናወን ላይ ያሉ ሥራዎች**

- ለ1991 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያና የግብርና ናሙና ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለየቅ/ጽ/ቤቶች ተልከው እየተሠራባቸው ነው።

- ከመስክ ለሚሰበሰቡ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃዎች የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቷል::

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃዎች ለማቀነባበር የሚያገለግሉ ማባዣዎች ለማዘጋጀት የሚያስችል በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሚገኙ ጠቅላላ ቤተሰቦችንና በግብርና ሥራ የተሰማሩ የግል ይዞታ ያላቸውን ቤተሰቦች ብዛት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሠንጠረዦች ተዘጋጅተዋል::

- በተባበሩት መንግሥታት የዓለም የምግብ ድርጅት (FAO) በኩል ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች በጥያቄዎቹ መሠረት መረጃዎቹ ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል::

- ለ1990 ከማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የተካሄደው የማዳበሪያ ቤንች ማርክ ጥናት መረጃዎች ተቀነባብረውና ተተንትነው ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል:: ሆኖም የጥናቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅት ለቀረቡ አንዳንድ ተጨማሪ የማሻሻያ ሃሳቦች እንዲካተቱ ተደርጎ ሪፖርቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል::

- ለ1990 ዓ.ም. በሐረሪ ክልል የተካሄደውን የግብርና ጥናት የሕዝብ ቆጠራ፣ የመሬት ስፋትና ምርት፣የመሬት አጠቃቀምና የምርት ግባቶችን በተመለከተ የተዘጋጀው ጥራዝ አንድ ሪፖሪት ተጠናቆ ታትሟል:: የዚሁ ጥናት አካል የሆነው ጥራዝ ሁለት ሪፖርትም ተጠናቆና ለጥናቱ ባለቤት ሁለቱም ጥራዞች በአንድነት እንዲላክ ተደርጓል::

- በ1993 ዓ.ም ለማካሄድ ለታቀደው የግብርና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራ በመሠራት ላይ ነው:: እንዲሁም ለዚሁ የግብርና ቆጠራ ሥራ ቅድመ ዝግጅት ይረዳ ዘንድ ከተለያዩ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች (የመንግሥት እርሻ፣ ኮሜርሻል ፋርምስንና የድርጅቶች ተቋማት እርሻዎችን) በተመለከተ ተፈላጊ መረጃዎችን የመሰብሰብ ተግባር እየተካሄደ ነው::

- ለግብርና ናሙና ጥናትና ለአጠቃላይ የግብርና ቆጠራ የማሳ ልከቶችን ሥራ በተሻሻለ መንገድ ሊያሰራ የሚችል የአለካከ ዘዴን GPS በሚባል መሣሪያ የሙከራ ልምምድ ተደርጓል:: ወደፊትም በተደጋጋሚ ተመሣሣይ ሙከራዎች ይደረጋሉ::

- በ1993 ዓ.ም ለሚካሄደው የግብርና ቆጠራ ቅድመ ዝግጀት ሥራ የሚውል የቆጠራ (Draft) ዶኩመንት ተዘጋጅቶ የመ/ቤቱ ማኔጅመንት ካፀደቀው በኋላ ዝርዝር ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችሉ መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ ለማኔጅመንት ቀርቧል::

- ለግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ሊያገለግሉ የሚችሉ የቋሚ ሰብሎችኘ የአትክልት ፍራፍሬ እንዲሁም የሥራ ሥር ተክሎችን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን በተመለከተ ለመነሻ ሃሳብ የሚሆን ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ይህንኑ በተግባር ለመተርጎም የመምሪያው ባለሙያዎች በወሎ፣ በአዲስ አበባና በሐረሪ ክልሎች ተደጋጋሚ ሙከራዎች(Pre-test) አድርገዋል:::

- በ1993 ዓ.ም ሊካሄድ ለታቀደው የግብርና ቆጠራ አጠቃላይ ቆጠራ (Complete Enumeration) ሳይሆን የናሙና ቆጠራ (Sample Enumeration) መሆን ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ አንድ ዶኩመንት አዘጋጅቶ አቅርቧል::

- ለግብርና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች የተለያዩ ኮሚቴዎችና ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነታቸው የሚገልጽ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን እነዚህም:-

  - የግብርና ቆጠራ የዝግጅት ሥራዎች አስተባባሪ ኮሚቴ
  - የግብርና ቆጠራ ግብረ ኃይል
  - የግብርና ቆጠራ የቴክኒክ ኮሚቴ ናቸው:: እነዚህ ኮሚቴዎች ባካሄዱዋቸው ስብሰባዎች ለመነሻነት ቀርቦ በነበረው የመረጃ ዓይነቶች ዝርዝር ላይ በመነጋገር ተጨማሪ የማሻሻያ ሀሳቦች እንዲካተቱ ከመደረጉም ሌላ ስምምነት ለተደረሰባቸው የመረጃ ዓይነቶች የመጠይቅ ዝግጅት በመከናወን ላይ ይገኛል::

- ለግብርና ቆጠራ ዝግጅት የሚረዳ በሀገሪቱ የሚበቅሉ ቋሚ ሰብሎችኘ አትክልቶችንና የሥራሥር ተክሎችን ዓይነትኘ የመትከያና የመሰብሰቢያ ወቅት ለማወቅ እንዲቻል በወረዳ ደረጃ ቅጽ ተዘጋጅቶ በቅ/ጽ/ቤቶች አማካይነት እንዲሰበሰብ የተደረገ ሲሆን በተመሣሣይ ሁኔታ የከብት እርቢ አካባቢ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ሊጠቁም የሚችል መረጃ በስድስት የከብት እርቢ ወረዳዎች በቅ/ጽ/ቤቶች አማካይነት እንዲሰበሰቡ ተደርጓል::

## 3.2 የቤተሰብ በጀትኘ የዋጋዎችና የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ ጥናትን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየጊዜው ዓለም አቀፍ የአሠራር ዘዴዎችን በመጠቀም የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በመሰብሰብና በማጠናቀር ውጤታቸው በወቅቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል:: በመሆኑም በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው::

### 3.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶች ሥራን በተመለከተ

#### ሀ. በከተሞች የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ

- የ1989 ከግንቦት እስከ ነሐሴ ድረስ ያለው መረጃ የሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል::

- የ1990 ከመስከረም እስከ ነሐሴ ድረስ ያለው መረጃ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል::

- ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ 1991 ያለው መረጃ የቅንብሩ ሥራ በማለቁ ሪፓርቱ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል::

- የጥር ወር 1991 መረጃ የዳታ ክሊኒንጉ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የዚሁ ዓመት የየካቲት ወር መረጃ ደግሞ የዳታ ኢንትሪ ሥራ አልቋል:: እንደዚሁም የመጋቢት ወር መረጃው ተሰብስቦ በሚቀጥሉት አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ወደ ዋና መ/ቤት ይሰበሰባል::

#### ለ. በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ

- የ1990 ከመስከረም እስከ ነሐሴ ድረስ ያለው መረጃ የቅንብሩ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ሪፖርቱም በሁለት መልክ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል:: የአንደኛው ሪፖርት ዝግጅት የሦስት ወር አማካይ የዋጋ መረጃ በዞን ደረጃ የያዘ ሲሆን ሪፓርቱም ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሠራጭ ተደርጓል:: ሁለተኛው ሪፖርት ግን የያንዳንዱን ወር መረጃ በዞን ደረጃ የሚያሳይና ሪፖርቱም በጥቂት ኮፒ ተዘጋጅቶ ለሪፈረንስ በቤተመጻሕፍት ውስጥ እንዲቀመጥ ተደርጓል::

- የ1991 ከመስከረም እስከ ኅዳር ያለው መረጃ ቅንብሩ ተጠናቆ ሪፓርቱ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል:: እንደዚሁም የታኅሣሥና የጥር 1991 መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ አልቆ የዳታ ክሊኒንጉ ሥራም እየተጠናቀቀ ነው:: የየካቲት ወር መረጃ የዳታ ኢንትሪው ሥራ ያለቀ ሲሆን የመጋቢት ወር ደግሞ ከመስክ መረጃው ተሰብስቦ በመጠናቀቁ ወደ ዋናው መ/ቤት እየተሰባሰበ ነው::

ሐ. <u>በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

- የ1989 ዓ.ም. የአምራች ዋጋ መረጃ ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- የ1990 ዓ.ም. መረጃ ሪፖርቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ወር 1991 ድረስ ያለው የአምራች ዋጋ መረጃ ሪፖርቱ ለሕትመት የተዘጋጀ ሲሆን የጥር ወር መረጃ ደግሞ የጸታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ የጸታ ክሊኒንግ ሥራ ተጀምሯል፡፡ የየካቲት ወር መረጃ የጸታ ኢንትሪ ሥራ ሲጠናቀቅ የመጋቢት ወርም መረጃ ከመስከ የመሰብሰቡ ተግባር በማለቁ መጠይቆቹ ወደ ዋናው መ/ቤት እየተሰባሰበ ነው፡፡

መ. <u>በከተማ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የአምራቾች ዋጋ ጥናት</u>

በመጋቢት ወር 1991 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙከራ ለሚካሄደው ለዚህ ጥናት የሥራ ፕሮግራም ከመውጣቱም ሌላ የዕቃዎችንና የአገልግሎቶች መጠንና ዓይነት ለመወሰን በየድርጅቶቹ በመዘዋወር ምክር ተጠይቋል፡፡ በተገኘውም አስተያየት መሠረት የመጠይቅ ዝግጅት እየተከናወነ ሲሆን የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ ዝግጅትም ጎን ለጎን እየተካሄደ ቢቆይም መ/ቤቱ ካጋጠመው የሰው ኃይል እጥረትና በጥናቶች መደራረብ ምክንያት ይህ የሙከራ ጥናት ለ1993 እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

ሠ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስን በተመለከተ</u>

I. <u>የአገር አቀፍ የገጠርና፣ የከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶች</u>

ከሐምሌ 1990 እስከ ጥር 1991 ዓ.ም ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚው የተሰራጩ ሲሆን የየካቲት ወር ኢንዴክስ ደግሞ በመሠራት ላይ ነው፡፡

## II. የአዲስ አበባ ከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ

ከሐምሌ 1990 እስከ የካቲት ወር 1991 ድረስ ያለው ወርሃዊ የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን የመጋቢት ወር ኢንዴክስ ደግሞ በመሠራት ላይ ነው::

### 3.2.2 የቤተሰብ ገቢ ፣ ፍጆታና ወጪን በተመለከተ

በ1991-92 ሊካሄድ ለታቀደው የቤተሰብ ፍጆታና ወጪ ጥናት የሥራ መርሀ-ግብር የጊዜ ሰሌዳ፣ የመረጃ ስብሳቢና የተቆጣጣሪ መመሪያ፣ እንደዚሁም የእርማትና የኮድ አሰጣጥንና መረጃ ወደ ኮምፕዩተር የማስገባት ፕሮግራም ከመነደፉም ሌላ የመጠይቅና የኮድ ቡክ ዝግጅት በመከናወን ላይ ነው::

### 3.2.3 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናትን በተመለከተ

የ1990 ዓ.ም. በኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት መረጃ ወደ ኮምፕዩተር የማስገባቱ ሂደት ተጠናቋል:: የማባዣ (Weight) ዝግጅትም እየተሰራ ነው::

### 3.2.4 የሰው ኃይል ጥናትን በተመለከተ

በ1991 በጀት ዓመት በብሔራዊ ደረጃ ሊካሄድ ለታቀደው የሰው ኃይል ጥናት የሥራ መርሀ-ግብር በመዘጋጀቱ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ማለትም መጠይቆች፣ ቅጾች፣ ሌሎች መመሪያዎችና ሎጂስቲክስና እንደዚሁም ሥልጠና የመስጠቱ ሥራ በመጠናቀቁ በመስክ መረጃ የመሰብሰቡ ሂደት በዚህ ወር ተከናውኗል:: የተሞሉ መጠይቆችም ከየቅ/ጽ/ቤቶች ወደ ዋናው መ/ቤት በመሰባበብ ላይ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም የመረጃው የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን ሠንጠረዦችና መረጃውን ለመተንተን ተዛማጅ የኮምፕዩተር ቅንብር የዝግጅት ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው::

## 3.3. ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ

- ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩት የዋጋ ጥናት መጠይቆችን በመከለስ የዕቃዎችና አገልግሎቶች የወቅቱን የገበያ ሁኔታ በሚያንፀባርቅ መልኩ ተዘጋጅቶ በ1991 ዓ.ም. ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል::

- የአዲስ አበባ ከተማ ከስፋቱና ከማደጉ አኳያ የገበያ ዋጋ መረጃ አሰባሰብ በዛው መልክ የጥናቱ ሽፋን በመጨመር የገበያ ስርጭትና ውሎ ግምገማና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴንም ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ከወዲሁ ጥልቅ ጥናት ተካሂዷል:: በዚሁ መሠረት የከተማው መረጃ አሰባሰብ ቀደም ሲል ከሚሠራበት ከአራት ገበያዎች (ዞኖች) ከመስከረም ወር 1991 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ አስራ ሁለት የጥናት ገበያዎች ከፍ በማድረግ በነዚሁ 12 ገበያዎች የገበያ ዋጋ መረጃ እየተሰበሰበ ነው::

- ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ካላቸው የሕዝብ ብዛትና የገበያ ስፋት አንድ ገበያ ብቻ ከማጥናት በጎንደር፣ በደሴ፣ በናዝሬት፣ በጅማ፣ በአርባምንጭና በሐረር ከተማዎች ሁለት ሁለት ገበያዎች ሲጠኑ በድሬደዋ ከተማ ደግሞ ሦስት ገበያዎች እንዲጠኑ ተደርጓል::

- በሌላ በኩል በገጠር የዋጋ መረጃ የሚሰበሰብባቸው የቆጠራ ቦታዎችን ቁጥር በመቀነስ (የመረጃውን ጥራትና ወካይነት በማይቀንስ መልኩ) የእርማትና ኮድ አሰጣጥ እንደዚሁም መረጃን ወደ ኮምፒዩተር የማስገባት ሥራን በማቀላጠፍ ብሎም ሪፖርቱን ለተጠቃሚው በወቅቱ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ የዋጋ ጥናት ከሚካሄድባቸው ቀድሞ 1400 በኋላም 980 ከነበሩ የቆጠራ ቦታዎች ውስጥ በናሙና 450ዎቹ ብቻ እንዲጠኑ ተደርጓል::

- ከዓለም ባንክ በተገኘ ዕርዳታ የገበያ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ ለአንድ ዓመት በአማካሪነት የሚመጡትን ኤክስፐርት የኮንትራት ውል ከመዘጋጀቱም ሌላ በመስከረም ወር 1991 ዓ.ም. ለ6 ቀን መጥተው በነበረ ጊዜ አስፈላጊው የሀሳብ ልውውጥና ምክክር ተደርጓል:: አማካሪው ከህዳር ወር 1991 ዓ.ም ጀምሮ ሥራቸውን ጀምረዋል::

## 3.4. የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.4.1 የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናትን በተመለከተ

#### ሀ. የ1989 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናትን በተመለከተ

- የአዲቲንግ፣ ኮዲንግና የመረጃ ቅንብር እንዲሁም የትንተና ሥራ ከመጠናቀቁም በላይ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የ1990 ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ እንዱስትሪዎች ጥናት አስፈላጊው ዝግጅት ማለትም የመጠይቅና አሞላል መመሪያዎች ክለሳ ተደርጎ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ከመሰጠቱም ሌላ በአሁኑ ወቅት መረጃው ከመስክ እየተሰበሰበ ነው።

#### ለ. የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናትን በተመለከተ

የ1989 መረጃ ተሰብስቦ በሠንጠረዥ መልክ በማጠናቀር በሪፖርት መልክ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። የ1990 መረጃም ከመስክ እየተሰበሰበ ነው።

#### ሐ. የ1990 የኮንስትራክሽን አጠቃላይ ቆጠራን በተመለከተ

የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን ዝርዝር በቅ/ጽ/ቤት በኩል ለማግኘት ደብዳቤ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተላልፎአል። ከንግድና ኢንደስትሪ ሚ/ር እና ከክልል 14 ንግድ፣ ኢንደስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የአዲስ አበባ ከተማ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ዝርዝር በመምሪያው በኩል ተሰብስቦ በኮንስትራክሽን ዓይነትና በካፒታል እንዲሁም በአድራሻ ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም ለጥናቱ የሚሆን መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ዝግጅት በመጠናቀቁ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል። መረጃውም ከመስክ ተሰብስቦ በማለቁ መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆችም ወደ ዋና መ/ቤት ገብተዋል።

### መ. የማዕድንና ቁፋሮ የሙከራ ጥናትን በተመለከተ:

ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያስፈልገው የማዕድን ምርቶች መረጃ ተሰብስቧል። እንደዚሁም ለ1990 የማዕድን ቁፋሮ የሙከራ ጥናት የሚሆን የድርጅቶች ዝርዝር ከመዘጋጀቱም በተጨማሪ ለጥናቱ የሚያስፈልገው መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቁ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለተቆጣጣሪዎች የሚሰጠውን ሥልጠና ከኮንስትራክሽን ጥናት ጋር እንዲሰጥ የተደረገ ሲሆን መረጃውም ከመስክ ተሰብስቦ በመጠናቀቁ መጠይቆቹ ወደ ዋናው መ/ቤት ገብቷል።

### ሠ. ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት (STATISTICAL ABSTRACT) ለሚደረግ ዝግጅት የሚሆን የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናቶች፣ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃና የማዕድን ምርት መረጃዎች በመቀነባበራቸው ለሕትመት ክፍል ተሰጥቶ በመታተም ላይ ናቸው።

## 3.4.2 የንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃን በተመለከተ

- የትራንስፖርት መገናኛ መጽሔት መረጃ በመረጃ አለመሟላት ምክንያት ተቋርጦ የነበረውን ሥራ እንደገና ለመጀመር የ1989 መረጃ የሠንጠረዥ ቅንብርና የትንተና ሥራ በመሠራት ላይ ሲገኝ የዚሁ ወቅት የውጭ ንግድ ስታቲስቲክስ የገቢና የወጪ መረጃ ተሰብስቧል።

- በ1991 በጀት ዓመት ሊካሄድ ታቅዶ የነበረው የመንገድ ትራንስፖርት የሙከራ ጥናት በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ መደራረብ ምክንያት ለሌላ ዓመት እንዲተላለፍ ተደርጓል። ሆኖም የመጠይቁን የመጀመሪያ ረቂቅ ከልዩ ልዩ መ/ቤቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች አውደጥናት በማዘጋጀት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ መጠይቁ ለሙከራ ጥናት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል።

- ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም ዘርፎች እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለሟላት ለተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙን የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል።

ሠንጠረዥ 1

## የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የ1991 የዘጠኝ ወራት

## የጥናቶች ፊዚካል ሥራ አፈጻጸም በመቶኛ

| ተ.ቁ | የጥናቶች ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1990 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የተከናወነ | የ1991 የዘጠኝ ወራት ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የግብርና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የ1991 የሰብል ትንበያ ጥናት | አዲስ | 12 | 88 | 88 | 100 |
| 1.2 | የ1991 የግብርና ናሙና ጥናት | " | 12 | 78 | 78 | 100 |
| 2 | የዋጋዎች ጥናት | | | | | |
| 2.1 | የ1990 የዋጋ ጥናት (የቅንብርና የሪፖርት ሥራ) | ነባር | 72.1 | 22.9 | 22.9 | 100 * |
| 2.2 | የ1991 የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት (በከተማ) | " | 5 | 40.8 | 40.8 | 100 |
| 2.3 | የ1991 የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት (በገጠር) | " | 5 | 40.8 | 40.8 | 100 |
| 3 | የሰው ኃይል ጥናት | አዲስ | 5 | 60 | 60 | 100 |
| 4 | የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት (የቅንብርና የሪፖርት ሥራ) | | | | | |
| 4.1 | የ1990 የኢኮኖ. ማኅበራዊ ደህንነት ጥናት | ነባር | 75 | 15 | 15 | 100 * |
| 5 | የጤናና አመጋገብ ጥናት (የቅንብርና ሪፖርት ሥራ) | | | | | |
| 5.1 | የጤናና አመጋገብ ጥናት | " | 70 | 20 | 20 | 100 * |
| 6 | የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት (የቅንብርና ሪፖርት ሥራ) | | | | | |
| 6.1 | የ1990 የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት | " | 65 | 10 | 10 | 100 * |
| 7 | የኮንስትራክሽን ጥናት | አዲስ | - | 65 | 65 | 100 |
| 8 | የማዕድንና ቁፋሮ ሙከራ ጥናት | " | - | 65 | 65 | 100 |
| 9 | የ1990 የዋጋዎች ኢንዴክስ (የሪፖርት ሥራ) | | | | | |
| 9.1 | የ1990 ብሔራዊ የዋጋ ኢንዴክስ | ነባር | 5.6 | 4.4 | 4.4 | 100 |
| 9.2 | የ1990 የገጠር የዋጋ ኢንዴክስ | " | 5.6 | 4.4 | 4.4 | 100 |
| 9.3 | 1990 የከተማ የዋጋ ኢንዴክስ | " | 5.6 | 4.4 | 4.4 | 100 |
| 9.4 | የ1990 የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | " | 5.6 | 4.4 | 4.4 | 100 |
| 10 | የ1991 የዋጋዎች ኢንዴክስ | | | | | |
| 10.1 | የ1991 ብሔራዊ የዋጋ ኢንዴክስ | ነባር | - | 35.5 | 35.5 | 100 |
| 10.2 | " የገጠር " " | " | - | 35.5 | 35.5 | 100 |
| 10.3 | " የከተማ " " | " | - | 35.5 | 35.5 | 100 |
| 10.4 | " የአዲስ አበባ" " | " | - | 46.2 | 46.2 | 100 |

* ወደ 1991 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎች በዕቅድ ያልተያዙ ቢሆንም ከክንውኑ ጋር የሚመጣጠን ዕቅድ ተቀምጧል::

## 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ

### 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚያካሂዳቸው ለተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችንና የአፈጻጸም መመሪያዎችን እንደዚሁም ለጥናቶቹ የሚዘጋጁት መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ብቃታቸውና ወካይነታቸውን ከወዲሁ በማረጋገጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያደርጋል። ከዚህ አኳያ በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የሚከተሉት ሥራዎች ተከናውነዋል።

ሀ. በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም እንዲሸፍኑ ለተወሰነላቸው ክልሎችና ዞኖች ተጨማሪ ናሙና የቆጠራ ቦታዎች መረጣ ተካሂዷል።

ለ. ለተለያዩ ጥናቶች የሚያገለግል የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ስርጭት ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

ሐ. ለ1991 ለበልግ ጥናትና ለግብርና ጥናት መረጃ የሚያገለግል raising factor የተዘጋጀ ሲሆን ይህንኑ raising factor ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት እንዲሁም ለጤናና አመጋገብ ጥናቶች እንዲያገለግል በተመሳሳይ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል። የቤት እንስሳት ጥናት raising factor ሥራም እየተካሄደ ነው።

መ. ለ1991 የግብርና ትንበያ ጥናት raising factor ከመዘጋጀቱም በተጨማሪ በ1991 ለሚካሄደው የማዕድን ቁፋሮ ጥናት ምርጫ ተካሂዶ ለዚሁ የሚሆን ኮድ ቡክ ተዘጋጅቷል።

ሠ. ለሰው ኃይል ጥናት በተከሞች ተጨማሪ የቆጠራ ቦታዎች ከመመረጣቸውም በተጨማሪ ለዚሁ ጥናት የሚያገለግል ኮድ ቡክ ተሠርቶ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል።

### 4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች

መ/ቤቱ በናሙና ጥናቶች የተለያዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያገለግሉና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አገልግሎት የሚውሉ ካርታዎች ከማዘጋጀቱም ሌላ የስታቲስቲክስ መረጃ ውጤቶች የሚያመለክቱ ልዩ ልዩ ግራፎች፣ ቻርቶችና ሥዕላዊ መግለጫዎች ይሠራል።እንደዚሁም

ለስታቲስቲክስ ጥናት የሚያስፈልጉ የአስተዳደር ክልሎችና የቦታ ስሞች፣ አዳዲስ ከተሞችና በገጠር የአሰፋፈር ሁኔታ (Settlement Pattern) ለመከታተል ይቻል ዘንድ የካርታዎችን ወቅታዊነት እየጠበቀ ያዘጋጃል:: በመሆኑም በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የሚከተሉትን አከናውኗል::

ሀ. በገጠር ለሚካሄደው የግብርና ጥናት አገልግሎት የሚውሉ 1503 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በማስፋት(enlarge) በA3 Size ወረቀት ተዘጋጅተዋል::

ለ. በሌሮይ ሕትመት የ20 ዞኖች ካርታዎች የተሠሩ ሲሆን 3 ወረዳዎች ባለ 50ሺ እስኬል ካርታ በሌሮይ ተሠርቷል::

ሐ. 1:250,000 ቶፖግራፊ ካርታዎች ዝርዝር በኢንዴክስ ቁጥራቸውን በሚሸፍናቸው ወረዳዎች ብዛትና ዝርዝር ለሁሉም ብሔራዊ ክልሎች ተለቅሞ በኮምፒውተር እንዲታተም ሲደረግ በተመሣሣይ ሁኔታ 150,000 ባለከለርና ጥቁርና ነጭ ካርታዎች በኢንዴክስ ቁጥር በሚሸፍን መልኩ ሠንጠረዥ ተሠርቶ ይህንኑ በካምፕዩተር ታትሞአል::

መ. የ199 የወረዳ ካርታዎች በአዲስ መልክ ቤዝማፕ ላይ የማስፈሩ ሥራ ከመጠናቀቁም በላይ የ189 ወረዳዎች የድንበር መስተካከል ተደርጎባቸዋል::

ሠ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃን ወደ አትላስ በመቀየር ሥራ ውስጥ እስካሁን የትግራይ ክልል በተለያዩ አርዕስቶች ላይ አትላስ ካርታዎች እየተሠሩ ነው::

## 5. <u>ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ፡-</u>

በየዓመቱ እየተዘጋጀ ለሚወጣውና የአገሪቷ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንደዚሁም ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመሰብሰቡ ሥራ ተጠናቋል:: በመሆኑም በዓመታዊ መጽሔቱ የሚካተቱ መረጃዎች ከሞላ ጎደል ተሰባስበው በመቅረባቸውና የሕትመቱ ሥራ በመጠናቀቁ መጽሔቱም በመጠረዝ ላይ ነው::

መጽሔቱ በሚዘጋጅበት ወቅት ተጠቃለው ከሚካተቱት በርካታ መረጃዎች ውስጥ፡-

- የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች ፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድን ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ (ፐብሊክ ፋይናንስ) መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንጻ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣ .... ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

# 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

## 6.1 የሰው ኃይል ሁኔታ

በ1991 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 388 ቋሚና 2276 የኮንትራት በጠቅላላው 2664 ሠራተኞች ነበሩ። ከነዚህ የሰው ኃይል ውስጥ 16 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 9 ሠራተኞች በሞት እንደዚሁም ሌሎች 14 ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ሥራ የለቀቁ ሲሆን 1 ሠራተኛ በዝውውር ወደ ሌላ መ/ቤት ሄዷል። ከዚህም ሌላ የ210 ሠራተኞች ቅጥር ተከናውኗል። በሌላ በኩል በዚህ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ 356 መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 23 የዳታ ኢንትሪ ሠራተኞች፣ 3 ዘበኞች፣2 የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች፣ 1 ረዳት የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪ ፣ 18 ሹፌሮች ፣1 ጀማሪ ተመራማሪና 1 ስታቲሺያን በድምሩ 405 የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ሲከናወን 202 ሠራተኞች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ ተሰናብተዋል።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ያለው የሰው ኃይል ብዛት 3,039 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 560 ብቻ ቋሚ ሠራተኞች ናቸው:: ጠቅላላ የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል::

<u>ሠንጠረዥ 2</u>

## <u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 388 | 2276 | 2664 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 210 | 405 | 615 |
| 3 | በዝውውር የመጡ | 2 | - | 2 |
| 4 | ወደሌላ መ/ቤት ተዛውረው የሄዱ | /1/ | - | /1/ |
| 5 | በጡረታ የተገለሉ | /16/ | - | /16/ |
| 6 | በሞትና በልዩ ልዩ ምክንያት ሥራ የለቀቁ | /23/ | /202/ | /225/ |
| | በሩብ ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ | 560 | 2,479 | 3,039 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 126 ባለሙያዎች፣ 165 መለስተኛ ባለሙያዎች፣ እና 269 የአስተዳደር የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው:: የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለይ 367 ወንዶች (65.5 በመቶ) ሲሆን 193 ደግሞ ሴቶች (34.5 በመቶ) ናቸው::

የኮንትራት ሠራተኞችን በተመለከተ ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት በተላለፈው ውሳኔ መሠረት እስከ ነሐሴ 1989 ዓ.ም ድረስ ያልተቋረጠ የ10 ዓመትና በላይ አገልግሎት ያላቸው የኮንትራት ሠራተኞች ቋሚ እንዲሆኑ በመወሰኑ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመነጋገር በተለያዩ የሥራ መደቦች ላይ የሚገኙ የ838 የኮንትራት ሠራተኞች ወደቋሚነት የማዘዋወሩን ሂደት ቀጥሎ የ820 ሠራተኞች ቅጥር የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ስምምነት እንዲያገኝ ተልኳል:: ከዚህ ውስጥ የ60 ኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር ስምምነት አግኝቶ የተመለሰ ሲሆን በጠቅላላው ከኮንትራት ወደ ቋሚ የተዛወሩ ሠራተኞች ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ለመክፈል እንዲቻል በየደመወዝ እርከኑ ተዘጋጅቷል:: ከዚህም በተጨማሪ የነዚሁ ሠራተኞች የትምህርትና የመጀመሪያ ቅጥር ማስረጃ ከማህደራቸው ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል::

ብዛታቸው 2295 /ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አምስት/ ለሚሆኑ የመስክ ሠራተኞችና ሥራቸው ከመስክ ሥራ ጋር የሚያንቀሳቅሷቸው ሠራተኞች የጥቅል የአደጋ ኢንሹራንስ የብር 443,114.43 ተገብቶላቸዋል።

## 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠና

የባለሥልጣኑ መ/ቤት እያደገ የመጣው የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ይችል ዘንድ በስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ፣ በመረጃ ቅንብር፣ ትንተናና በፕሮጀክት ዝግጅት እንደዚሁም በሌሎች ተመሣሣይ ሥራዎች ብቁ ባለሙያ ለማግኘትና ያላቸውን ዕውቀት ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በዚህ ዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተለው ተከናውኗል።

- ለዋጋዎችና ለግብርና ጥናቶች በዋናው መ/ቤት ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች እና ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ከሐምሌ 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ለ8 ቀናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ አሰልጣኞች ወደ ቅ/ጽ/ቤቶች በመሄድ ለተቆጣጣሪዎችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች ከነሐሴ 4 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ለ12 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በ1990 የተሰበሰበውን የጤናና የአመጋገብ ጥናት መረጃ ለቅንብር ሥራ ይረዳ ዘንድ የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ በማዘጋጀት ለኤዲተሮችና ኮደሮች በሐምሌ ወር 1990 ዓ.ም የ3 ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የመረጃ ቅንብር በቅ/ጽ/ቤቶች እንዲጀመር በነበረው ዕቅድ መሠረት ለጊዜው በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች (በናዝሬት፣ ጅማ፣ አዋሳና ሐረር) ለተቀጠሩ ሠራተኞች የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ የዳታ ኢንትሪ እና የዲስኬት መለያ ቁጥር መስጠት(Labeling) ፕሮግራም ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በ1991 በጀት ዓመት ለተካሄደው የኮንስትራክሽንና የማዕድን ቁፋሮ ጥናቶች በሥራው ላይ ለሚሳተፉ ኃላፊዎች፣ ተቆጣጣሪዎች ፣ መረጃ ሰብሳቢዎችና ኤዲተሮች ከጥር 3 እስከ 12 አሥር ቀን የወሰደ ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የሰው ኃይል ጥናት(Labor Force Survey) በተመለከተ ደግሞ በሥራው ላይ ለሚሠማሩ በተለያዬ ደረጃ ላሉ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ለስድስት ቀን በቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ለ10 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። እንደዚሁም በትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ለሚሠማሩ ሠራተኞች አምስት ቀን የፈጀ ስልጠና ወስደዋል።

- በአገር ውስጥ በሚሰጥ ሥልጠና ማለትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 3 ሠራተኞች ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም በ1990 የጀመሩት ሥልጠና በዚህ ዓመትም የቀጠሉ ሲሆን በተመሣሣይ ሁኔታ ሌሎች 3 ሠራተኞች በ1991 ለማስተርስ ዲግሪ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ እየተማሩ ነው:: እንደዚሁም 8 ሠራተኞች ለማስተርስ ዲግሪ፣ 1 ሠራተኛ ደግሞ ለዲፕሎማ ወደ ተለያዩ አገሮች ተልከው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው::

## 7. የበጀት አጠቃቀም

ለ1991 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 50,581,900.00 የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 11,708,000.00 ፣ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 38,873,900.00 የተፈቀደ ነው:: ከተፈቀደው ጠቅላላ በጀት መሀል 23.15% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን ፣ 76.85% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው::

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው መደበኛ በጀት በሚከተሉት የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው:: ይኸውም:-

- ለደመወዝ ................................... ብር 10,104,800.00
- ለውሎ አበል ................................ " 41,300.00
- ለሥራ ማስኬጃ.............................. " 1,156,900.00 የተያዘ ነው::

ለዚህ ዓመት ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ውስጥ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው መጠን እንደሚከተለው ቀርቧል::

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ከሐምሌ 1/90 እስከ መጋቢት 30/91 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 3,438,118.64 ሲሆን ብር 3,292,030.04 (95.75%) ወጪ ሆኗል::

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ውስጥ በዘጠኝ ወራት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 14,198.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 17,083 ወይም 120.32 በመቶ ነው::

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 658,212.23 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 567,787.76 ነው አፈጻጸሙ ከተፈቀደው ጋር ሲነጻጸር 86.26 በመቶ ነው::

ከሐምሌ 1 ቀን 1990 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1991 ድረስ ወጪ የሆነው ብር 3,876,900.27 በእጅ ገቢ ከሆነው ብር 4,096,330.87 ጋር ሲነጻጸር 94.64 በመቶ ሆኗል:: አኃዛዊ መረጃው በሠንጠረዥ 3 ሠፍሯል::

ለ. <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው የካፒታል በጀት በሚከተለው ሁኔታ የተከፋፈለ ነው:: ይኸውም:-

- ለተቀናጀ ብሔራዊ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 23,927,100.00
- ለግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ብር 14,946,800.00 ነው::

ከሐምሌ 1 ቀን 1990 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1991 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ብር 20,077,500 ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ገቢ የሆነ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ወጪ የሆነው ብር 20,731,617.00 ነው::

ይኸውም ወጪ የሚከተሉትን ያጠቃልላል:-

- ለቤተመጻሕፍት ሕንጻ ማሠሪያ............ ብር 506,213.-
- ለዕቃዎችና መሣሪያ........................ ብር 6,800.-
- ለደመወዝ.................................. ብር 7,640,300.-
- ለሰው ጉልበት ወጪ........................ ብር 1,543,400.-
- ለሥራ ማስኬጃ............................. ብር 10,204,031.-
- ለኢንሹራንስ (ለሠራተኞች)................. ብር 443,114.-
- ለኢንሹራንስ( ለተሽከርካሪዎች)............ ብር 387,759.-

በ1991 በጀት ዓመት የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ሥራ ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንደሚጀመር ዕቅድ ቢኖርም በሌሎች ተደራራቢ ሥራዎች በተባለው ጊዜ ሊጀመር ባለመቻሉ የበጀት እንቅስቃሴውም በዚህ ሪፖርት አልተካተተም::

የመደበኛና የካፒታል በጀትን በተመለከተ በአጠቃላይ ከሐምሌ 1 ቀን 1990 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1991 ድረስ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 24,173,830.87 ወጪ

ከሆነው ብር 24,608,517.27 ጋር ሲነጻጸር 101.80 በመቶ ሆኖአል:: አኃዛዊ መረጃው በሠንጠረዥ 3 ላይ ተመልክቷል::

ሠንጠረዥ 3

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1991 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በጀት አጠቃቀም

| ተራ ቁ. | የበጀት አጠቃቀም | ለ1991 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተጠቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት (በ03 እና 04) |
|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 1 | መደበኛ በጀት | 11,708,000.00 | 4,096,330.87 | 3,876,900.27 | 219,430.6 |
| 1.1 | ለደመወዝ | 10,104,800.00 | 3,438,118.64 | 3,292,030.04 | 146,088.6 |
| 1.2 | ለውሎ አበል | 41,300.00 | 14,198.00 | 17,083.00 | /2,885.0 |
| 1.3 | ለሥራ ማስኬጃ | 1,561,900.00 | 658,212.23 | 567,787.76 | 90,424. |
| 2 | ካፒታል በጀት | 38,873,900.00 | 20,077,500.00 | 20,731,617.00 | /654.11 |
| 2.1 | ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም | 23,927,100.00 | 20,077,500.00 | 20,731,617.00 | /654.11 |
| 2.2 | ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት | 14,946,800.00 | - | - | - |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **50,581,900.00** | **24,173,830.87** | **24,608,517.27** | /434,686.4 |

* በእጅ ከገባው በልዩነት (በመብለጥ) የተከፈለው ለሌሎች ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በእርዳታ ከተገኘው ገንዘብ ሲሆን ይህም የገንዘብ ሚኒስቴር ተሟልቶ ሲፈቀድ ተተኪ የሚሆን ሂሣብ ነው::

## 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚካሄዱት ጥናቶች በተያዘላቸው ፕሮግራም መሠረት እንዲከናወኑና እነዚሁኑ ክንውኖች የተቀላጠፉ እንዲሆኑ እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ ሥራዎችን ያከናውናል:: በዚሁ መሠረት በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

ከሐምሌ 1 ቀን 1990 እስከ መጋቢት 30 ቀን 1991 ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ ብር 2,975,760.84 ወጪ በማድረግ የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ግዢ የተፈጸመ ሲሆን ዝርዝሩ በሠንጠረዥ 4 ሰፍሯል::

ሠንጠረዥ 4

## ለመኪናዎች ጎማ፣ ለነዳጅና ለልዩ ልዩ ዕቃዎች ግዢ የዋለ ወጪ

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ወጪ (በብር) |
|---|---|---|
| 1 | ለልዩ ልዩ ጎማዎች ግዢ | 278,838.75 |
| 2 | ለመኪናዎች መለዋወጫና ጥገና | 1,791,218.91 |
| 3 | ለነዳጅና ቅባት | 728,980.02 |
| 4 | ለጽሕፈት መሣሪያ | 74,762.15 |
| 5 | ለሕንጻና ኤሌክትሪክ ዕቃዎች | 11,513.08 |
| 6 | ለቢሮ ዕቃዎች | 40,594.96 |
| 7 | ለጽዳት ዕቃዎች | 1,870.40 |
| 8 | ለልዩ ልዩ | 47,982.57 |
| | **ድ ም ር** | **2,975,760.84** |

## 8.2 የቤተ መጻሕፍትና የሠራተኛ ክበብ ግንባታ እና የዕቃዎች ጥገናን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

### 8.2.1 የቤተመጻሕፍትና የሠራተኛ ክበብ ግንባታ

ለባለሥልጣኑ መ/ቤት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ቤተመጻሕፍትና ክበብ በአንድነት አንድ ፎቅ ያለው ሕንጻ እንዲሠራ በመፈቀዱ ሥራው በ1990 መጨረሻ አካባቢ ተጀምሮ እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ሥራ ብር 506,213.00 ወጪ ሆኗል፡፡

### 8.2.2 የዕቃዎች ጥገናን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

- በአገልግሎት ብዛት ሥራ አቋረጠው የነበሩ የስልክ መስመሮች ከቴሌኮሚኒኬሽን ጋር በመነጋገር 5 ቀጥታና 9 የውስጥ መስመሮች ተስተካክለው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት በሁለት ቦታ የሚገኙት የመጸዳጃ ክፍሎች በመበላሸታቸው የነበረውን ከፍተኛ ችግር ለማስወገድ በተወሰደው እርምጃ

ብር 7633.65 (ብር 4203.65 ለዕቃ ግዢ፣ ብር 3430.00 ለእጅ ዋጋ) ወጪ በማድረግ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ሆኗል::

- በዋና መ/ቤት ግቢ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው የሠራተኛ ክበብ ከቤተመጽሐፍት ጋር እንዲሰራ በመፍረሱ የመ/ቤቱ ሠራተኛ ሻይ ፍለጋ ከመ/ቤቱ ውጪ ይሄድ ስለነበረ በአሁኑ ወቅት ከግቢ ጊዜያዊ ሻይ ቤት እንዲሰራ በመደረጉ ሠራተኛው በሥራ ሰዓት እንዳይወጣ መፍትሔ አስገኝቷል::

## 8.3 የመኪና ሥምሪትና ጥገናን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

- በዋናው መ/ቤት ተመድበው የሰርቪስ አገልግሎት ከሚሰጡት 19 አውቶሞቢሎች በተጨማሪ 135 የመስክ መኪናዎች በ22ቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ተመድበው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው::

- በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት ከሚሰጡት መኪናዎች ውስጥ በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 70 መኪናዎች በጋራዥ ለማስጠገን ብር 1,449,438.55 ለመለዋወጫ ዕቃዎችና ለአገልግሎት ወጪ በማድረግ ክፍያ ከመደረጉም በተጨማሪ በዋናው መ/ቤት ጥገና ለተካሄደላቸው መኪናዎች መለዋወጫ መግዣ ብር 341,786.36 ወጪ ተደርጓል::

- ለመኪናዎች ጥገና ለቅባትና ነዳጅ ብር 728,980.02 ወጪ ከመደረጉም ሌላ ብር 594.00 ለጎማ ጥገና ወጪ ሆኖ በማሰራት መኪናዎቹ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል::

## 8.4 የኢንሹራንስ አገልግሎትን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት አዲስ ለገዛቸው 29 አዳዲስ የመስክ መኪናዎች የኢንሹራንስ ዋስትና እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን የቆዩት ነባር መኪናዎች ደግሞ እ.ኤ.አ. ጥር 1/1999 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት የኢንሹራንስ እደሳ ተደርጎላቸዋል::

- በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 7 መኪናዎች በብር 24,853.18 በጋራዥ ተጠግነው ይህንኑ ወጪ በኢንሹራንስ ተሸፍኗል::

- ብዛታቸው 2295 ለሚሆኑ የመስክ ሠራተኞችና ከመስክ ሥራ ጋር የሚንቀሳቀሱ ሌሎች ሠራተኞች የጥቅል የአደጋ ኢንሹራንስ በብር 443,114.43 ተገብቶላቸዋል፡፡

## 8.5 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት የወቅቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል የሀገሪቱን የፌደራል ሥርዓትና አደረጃጀት በመከተል ከዚህ በፊት ከነበሩት ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ በአምስት ብሔራዊ ክልሎችና በሌሎች አምስት ዞኖች ላይ ቅ/ጽ/ቤቶች ከፍቷል፡፡ ለእነዚህ ተጨማሪ ቅ/ጽ/ቤት አገልግሎት የሚሰጥ ቢሮ (ቤት) ለማግኘት ለክልል፣ ለዞንና በየደረጃው ለሚገኙት ምክር ቤቶች መ/ቤቱ ባቀረበው ተደጋጋሚ ጥያቄ መሠረት በሚዛን ተፈሪ፣ በድሬደዋና በአምቦ ከኪራይ ነፃ የሆኑ ቢሮዎች የተገኙ ሲሆን በጅጅጋ፣ በጋምቤላ ፣ በአሶሳ፣ በአሳይታ፣ በደብረብርሃንና በሆሳዕና ደግሞ በኪራይ ቢሮዎች ተገኝተዋል፡፡ ሆኖም እስካሁን ድረስ ቢሮ በማፈላለጉ ጥረት ሂደት ላይ የሚገኘው የአሰበ ተፈሪ ቅ/ጽ/ቤት ሲሆን የባሕርዳር ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ እስካሁን ቢሮ ባለመገኘቱ በደብረማርቆስ ከተማ ባለው ቅ/ጽ/ቤት በኩል እየተሠራ ነው፡፡

- ለነዚህ አዲስ ለተከፈቱት ቅ/ጽ/ቤት ተጠሪዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባር እንዴት መወጣት ይችላሉ በሚል ርዕስ ውይይት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር ከመካሄዱም በተጨማሪ ይህን ለማስፈጸም የወጡት ደንቦችና መመሪያዎች ቅጂ ተሰጥቶዋቸዋል፡፡

- እነዚህንና ሌሎችም ቅ/ጽ/ቤቶችን በሰው ኃይል ለማደራጀት በነበረው ዕቅድ የሂሣብ፣ የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞችና ገንዘብ ያዦች ቅጥር ከመከናወኑም ሌላ ለአዳዲስ ቅ/ጽ/ቤቶች የGov ባንክ ሂሣብ ቁጥር በመክፈትና አስፈላጊው የጽ/ቤት መሣሪያ በማደራጀት መደበኛ ሥራቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ተደርጓል፡፡

- የየቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች በዋናው መ/ቤት በመገኘት በ1990 በጀት ዓመት በተካሄዱ ጥናቶች እና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ሪፖርት አቅርበው ውይይት በማካሄድ መፍትሄዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በ1991 ለሚካሄዱት ጥናቶች ይዘትና ጥራት በተመለከተ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

- የData Processing Decentralization ሂደት ውስጥ ለመጀመሪያ ዙር በተመረጡ አራት ቅ/ጽ/ቤቶች ( ናዝሬት፣ አዋሳ፣ ጅማና ሐረር ) የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ የዳታ ኢንትሪ፣ የዳታ ክሊኒንግ እና የዲስኬት ሌቤሊንግ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው የኮምፒዩተር ባለሙያዎች በሥፍራው በመገኘት ሥልጠና ሰጥተዋል። የሙከራ ሥራውም በአራቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ተጀምሮ የተከናወነ ሲሆን እስካሁን የ1991 የሰብል ምርት ትንበያ፣ የመኸር ወቅት ጥናትና የቤት እንስሳት ጥናት መረጃዎች ኤዲቲንግና ዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል። ከዚህም ሌላ መረጃዎችን በቀጥታ በሞደም አማካኝነት ለማስተላለፍ እንዲቻል ለናዝሬት ቅ/ጽ/ቤት የሙከራ ሥራ ተጀምሯል።

- የሕትመት አገልግሎትን በተመለከተ እጅግ በርካታ የሕትመት ሥራዎች በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ተከናውነዋል። ከነዚህም ውስጥ ሕዝብና ቤት ቆጠራን በሚመለከት አገር አቀፍ ይዘት ያላቸው Summary እና Analytical ሪፖርቶች፣ የተለያዩ ጥናቶች የሚካሄድባቸው መጠይቆች፣ የመረጃ ሰብሳቢና የተቆጣጣሪ መመሪያዎችና በመ/ቤቱ የሚሠራባቸው በርካታ ቅጾች ከሚጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በዚህም መሠረት ከሐምሌ 1990 እስከ መጋቢት 30/1991 ድረስ አጠቃላይ ብዛታቸው 4,640,177 A4 size ገጽ የሆኑ የተለያዩ መጽሔቶችና ጥራዞች ተሠርተዋል። እነዚህም ለመ/ቤቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚያገለግሉ ፎርሞችና ፐብሊኬሽኖች ይጨምራል።

- የጥናቶቹ ውጤት አስተማማኝ መለኪያ ስታቲስቲክስ (CV) ለ1990 የእንስሳት ናሙና ጥናት ፣ ለArea እና Production ጥናት ፣ ለ1990 የበልግ ምርት ጥናት .... ወዘተ ተሠርቷል።

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ሪፖርቶች በነጻ ዕደላና በሽያጭ መልክ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ያሠራጫል። በመሆኑም በዚህ ዘጠኝ ወራት ውስጥ 8131 መጽሔቶች ለመንግሥት መ/ቤቶችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች የታደሉ ሲሆን 3,143 መጽሔቶች ደግሞ በሽያጭ በብር 62,634.61 ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭተዋል።

- 134 የወረዳ ካርታዎች ታትመውና ኮፒ ተደርገው ካርታ እንዲሸጥላቸው ለጠየቁ በብር 10,208.00 ተሽጠዋል።

- ስታቲስቲካዊ መረጃ እንዲሰጣቸው ለጠየቁ መንግሥታዊ ለሆኑና ላልሆኑ መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ ተመራማሪዎች፣ ተማሪዎች፣... ወዘተ. ተሰጥቷል።

## 9. በእቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎች

1) አዲሱ የመ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ሣይፈቀድ ረዘም ላሉ ዓመታት በመዘግየቱ ምክንያት ፕሮፌሽናሎችን ጨምሮ ልምድ ያካበቱ በርካታ ሠራተኞች በፈቃዳቸውና በልዩ ልዩ ምክንያቶች መ/ቤቱ ከነበረው የሰው ኃይል ተቀንሰዋል:: ስለሆነም በጎደለውና ተፈላጊውን የሰው ኃይል በማሟላት ረገድ የሚከተሉት ጉዳዮች ውሣኔ ማግኘት ይኖርባቸዋል:: እነዚህም:-

ሀ. በአዲሱ ድርጅታዊ መዋቀር የሰው ኃይል ድልድልን አስመልክቶ የቀረበው ጥያቄ በአብዛኛው ተቀንሶ ስለተፈቀደ በተለይም መ/ቤቱ ካለበትና ወደፊትም ከሚጠበቅበት የሥራ ብዛትና ክብደት አንጻር የፕሮፌሽናል ሠራተኞች ብዛት በተፈላጊው መጠን መሠረት እንዲፈቀድ ለሚመለከታቸው አካላት መቅረብ ይኖርበታል::

ለ. ብዛት ያላቸው የኮንትራት ሠራተኞች በቋሚ ሠራተኛነት እንዲቀጠሩ በተወሰነው መሠረት ተግባራዊ እየሆነ ነው:: ስለሆነም የሥራው ስፋት በመጨመሩና የሠራተኞች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚከታተልና የሚያስፈጽም አካል በየቅ/ጽ/ቤቱ መመደብ ስለሚያስፈልግ በተለይም የአስተዳደር፣ የፋይናንስና የፐርሶኔል የሥራ መደቦች እንዲፈቀዱ ጥያቄው ለሚመለከታቸው አካላት ቀርቦ እንዲወሰን ያስፈልጋል::

ሐ. ከመ/ቤቱ በፈቃዳቸው የሚለቁት ባለሙያዎች ብዛት እየጨመረ ከመሄዱም በላይ በቅጥር ለማሟላት በሚሞከርበት ወቅትም የተፈለገውን ያህል ማግኘት አልተቻለም:: ስለዚህ ያሉትን ሠራተኞች ለማቆየትና ተፈላጊውንም ባለሙያዎች ለመቅጠር እንዲቻል ለመ/ቤቱ የተለየና የተሻለ የደመወዝ እስኬል ማስፈቀድ ያስፈልጋል::

መ. የተጓደሉ ሠራተኞችን በቅጥር ለማሟላት ተሞክሮ አጥጋቢ ውጤት አልተገኘም:: ለዚሁም በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ በሚገኘው የደመወዝስኬል ለመቅጠር እንዲቻል ውሣኔ ቢሰጥበት ጊዜያዊ መፍትሄ እንደሚሆን ይገመታል::

2) የመስክ ተሽከርካሪ መኪናዎች ፍላጎት በየጊዜው ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው። በዚሁ መሠረት በ1991 በጀት ዓመት እንዲገዙ የተፈቀዱ መኪናዎች ግዢ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በኩል ስለሚፈጸምና ሂደቱ አዝጋሚ እንደሚሆን ካለፈው ተመክሮ ለመረዳት ተችሏል። በያዝነው በጀት ዓመት ለተፈቀደው የመኪናዎች ግዢ የጨረታ አሸናፊውን ኩባንያ ለይቶ ለማሣወቅ ረዥም ወራት የወሰደ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት መ/ቤቱ ከአሸናፊው ኩባንያ ጋር ኮንትራት ተፈራርሞና L/C ከፍቶ የግዢውን ሂደት ለማፋጠን ሙከራ እየተደረገ ነው።